# በስራ ባሕል ሕዳሴያችን ላይ የተወረወረ ትርጉም አልባ ትችት

*ኢ.ብሳ ነመራ 7/16/12*

ዕውቀት አቅም ነው፡፡ ቁሳዊ ሐብት፣ መፍጠር የሚስችል፣ ቁሳዊ ሀብት ሊፈጠርበት የሚችልበትን ሁኔታ የሚያደላድል ዕምቅ አቅም፡፡ ይህ ዕምቅ አቅም እንደሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች በብላሽ የተሰጠ አይደለም፡፡ ራሱ ዕምቅ ሀብቱ መፈጠር ይኖርባታል፡፡ ይህ ደግሞ ዕምቅ ዕውቀቱን የሚፈጥረውን ሰው ጥረት ብቻ የሚሻ አይደለም፡፡ በተለይ ስርዓት የተበጀለት ዕውቀት/ ትምህርት የሚሰጥበት ሁኔታ ከፍተኛ ኢንቨስትመንትን ይጠይቃል፡፡

ይህ ዕምቅ ዕውቀት አንድ አገር የምትገኝበትን ሁኔታና መፃኤ እጣ ፈንታም ይወስናል፡፡ አንድ ሀገር በዜጎቿ ላይ ያላትን ዕምቅ ዕውቅት በማየት ቀጣይ ዕጣ ፈንታዋን መተንበይ ይችላል፡፡

ዕውቀት ለአንድ አገር ዕድገት ወሳኝ ግብአት በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ለትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ለዚሁ ዘርፍ እድገት ከፍተኛ መጠን ያለው ሃብት ኢንቨስት አድርጓል፡፡

በተለይ ከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ ቀደም ሲል ከሁለትና ሶስት የማይበልጡት ዩኒቨርሲቲዎች አሁን ቁጥራቸው ከሰላሳ በላይ ደርሷል፡፡ ቀደም ሲል ከአስር ሺህ በታች የነበረው የከፍተኛ የትምህርት የቅበላ አቅማቸውም አሁን ወደ 80 ሺህ ደርሷል፡፡ በየአመቱ ከዩኒቨርሲቲዎች ትመህርታቸውን አጠናቀው የሚወጡት ዜጎች ቁጥርም የዛኑ ያህል እያደገ ይገኛል፡፡በያዝነው ዓመት ከመንግስት ከፍተኛ የትመህርት ተቋማት ተመርቀው የሚወጡት ተማሪዎች ቁጥር ከ50 ሺህ በላይ ነው፡፡

በዚህ ዙሪያ በተለይ ከዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ከሚጠብቃቸው የሥራ ዕድል ጋር በተያየዘ ሰሞኑን የመገናኛ ብዙሃንና የተወሰኑ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ የአንዳንድ የግል መገናኛ ብዙሃንና የተቃዋሚ ፖለቲከኞቹ አስተያየት መነሻ በተለይ ከዚህ ቀደም የከፍተኛ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ የተወሰኑ ተማሪዎች በኮብል ስቶን፣ በግብርናና መሰል ስራዎች ላይ ተሰማርተዋል በሚል በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የቀረቡ ፕሮግራሞች እንደሆኑ ነው የተገለፀው ፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑና ፖለቲከኞቹ ከሰጡዋቸው አስተያየቶች መሃከል የተወሰኑትን መዘን ከነባራዊው ዕውነታ አኳያ እንመልከታቸው፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣ በሰኔ 24/2004 እትሙ "የትምህርት ፖሊሲ ምን እያፈራ ነው? ድንጋይ ጠራቢ ወይስ ባለሙያ?" በሚል ርዕስ በፖለቲካ አምዱ ካቀረበው ዘገባ እንጀምር፡፡

የሪፖርተር ዘገባ በሀገሪቱ የሰው ኃይል ማፍራት የሚችሉ ዩኒቨርሲቲዎች መገንባታቸው በበጎ ጎኑ የሚጠቀስ ተግባር መሆኑን አውስቶ፣ ተማሪዎቹን የማስተማር አቅም ያላቸው መምህራን

አለመኖራቸውን እንደችግር ያነሳል፡፡ “በቂ ዝግጅት ባልተደረገበትና ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን በበቂ ባልተሟሉበት ሁኔታ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በለብ ለብ እንዲመረቁ መደረጉ በአገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ የሚፈጥረው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም” ይለናል፡፡

እርግጥ ነው እውቀት የመፍጠር ስራ፣ በቂ ዕውቀት ባላቸው መምህራን ብቻ ሊከናወን የሚችልና የሚገባ ስራ ነው፡፡ እውቀት የሌለው መምህር ተማሪዎችን ማሳወቅ አይችልም፡፡

ወደ ሃገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስንመጣ አሁን ባሉት ከ30 በላይ የሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ቁጥር የሚፈለገውን ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር ሁለት ወይም ሶስት ብቻ በነበሩበት ከሃያ አመታት በፊት ከነበረው ጋር ስናነፃፅረው የአሁኑ የተሻለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከሁለት አስርት አመታት በፊት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው የዩኒቨርሲቲ መምህራን - ለዛውም ጀማሪ መምህራን ለመመረቅ በዝግጅት ላይ ያሉ ተማሪዎችን ጨምሮ ከአንድ በላይ ኮርሶችን ይሰጡ እንደነበረ በወቅቱ በትምህርት ላይ የነበሩ ዜጎች የሚያስታውሱት ዕውነት ነው፡፡

በወቅቱ የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት በአገሪቱ ውስጥ ስለማይሰጥ የውጭ የትምህርት ዕድሉን አግኝተው ደረጃቸውን የሚያሻሽሉ መምህራን ቁጥርም በጣም ጥቂት ነበር፡፡ በዚህ ደረጃ ለመማር ወደ ውጭ አገር ከሚላኩት መሃከል ወደሃገር ቤት የሚመለሱትም የተወሰኑት ብቻ ነበሩ፡፡ አንድ መምህር የመጀመሪያ ዲግሪውን ሳያሻሻል ለአስር አመትና ከዚያም በላይ የሚያገለግልበት ሁኔታ እንግዳ አልነበረም፡፡

አሁን ያለውን ሁኔታ ከዚህ ጋር ስናነፃፅረው የተሻለ ነው፡፡ አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ጀማሪ መምህር ሁለተኛ ዲግሪ ሳይዝ በመምህርነት የሚቆየው አንድ ቢበዛ ሁለት አመት ነው፡፡ የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪዎች በአገር ውስጥ መሰጠት መጀመሩ ነው ይህን ያሻሻለው፡፡

አሁን ያለው ሁኔታ ቀደም ሲል ከነበረው የተሻለ ነው ማለት ግን፣ የሚፈለገው ደረጃ ላይ ተደርሷል ማለት አይደለም፡፡ አሁንም ይቀራል፡፡ ሆኖም ችግሩን በአጭር ግዜ ውስጥ የማቃለል አቅም ተፈጥሯል፡፡ ያም ሆነ ይህ ችግሩ አለ የሚለው ትዝብት እውነትና ተገቢ ቢሆንም፣ የታየው መሻሻልና ዘላቂ ተስፋው ግን መዘንጋት የለበትም ፡፡

ይሄው የሪፖርተር ዘገባ “የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚወጡ ተማሪዎች እውቀትና ችሎታው ቢኖራቸው እንኳን፣ በቂ የስራ ዕድል ያገኛሉ ወይ?” የሚል ጥያቄ ያነሳል፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስነው የአንድ አገር መፃኤ እጣ ፈንታ  ልማት ወይ ውድቀት፣ብልፅግና ወይ ድህነት ባላት የተማረ የሰው ኃይል መጠንና ዓይነት ይወሰናል፡፡ ትምህርት /ዕውቀት በአንድ አገር መፃኤ እድል

ላይ ወሳኝ ድርሻ ስላለው፣ ሀገርን የማስተዳደር ኃለፊነት ያለበት መንግስት አንድና ሁለት አመታትን እያሰበ ሳይሆን በረጅም ግዜ ውስጥ አገሪቱ ሊኖራት የሚገባትን የሰው ኃይል ልማት ስትራቴጂ ቀርፆ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የህዝብን ሀብት ኢንቨስት ያደርጋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ከሰላሳ የሚበልጡ ዩኒቨርስቲዎችን አቋቁሞ፣ በአንድ ዙር በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ተማሪዎች አስተምሮ የአገሪቱን የዕውቀት አቅም ለማዳበር ሲነሳ፤ "ዘንድሮ፣ ከርሞ፣ በሁለት ምናልባት ሶስትና አራት አመታት የተፈጠረውን የዕውቀት አቅም ሙልጭ አድርጌ እጠቀማለሁ" በሚል ግምት አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ፣ የእድገት ግስጋሴውን ተከትሎ የሚፈጠረው የሰው ኃይል ፍላጎት የዕውቀት እጦት ተግዳሮት ሳይሆንበት በአንድ በኩል ክምችቱን እየተጠቀመ እንዲዘልቅ፤በሌላም በኩል የተማረው የሰው ኃይል ተቀጥሮ መስራትን ብቻ ሳይተማመን ራሱም ሥራ ፈጣሪ እንዲሆን ታስቦ እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎችን ተቀብሎ በነፃ እያሰለጠነ የሰው ኃይል አቅም ክምችቱን ያዳብራል፡፡ የመንግስት ስጋት የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት አንድ ቦታ ላይ የሰው ኃይል እጥረት እንዳይገጥመው ነው፡፡ በተለይ ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ለሆኑት የሳይንስና የኢንጂነሪንግ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የማህበራዊ ሳይንስ፣ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎች የቅበላ አቅም ጥምረት 30፡70 እንዲሆን ማድረጉ ይህን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ መንግስት የተማረ የሰው ኃይል ሲፈጥር ዘላቂ የእድገት አቅም መፍጠር ላይ አተኩሮ መሆኑ መታሰብ አለበት፡፡

ይህ ሁኔታ ከአጭር ግዜ አኳያ ሲታይ እንደተመረቁ በሰለጠኑበት ሙያ የመሰማራት ዕድል የማይገጥማቸው ተማራዊች ሊፈጥር የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ የሪፖርተር ዘገባ  የአገሪቱን የሰው ኃይል ፈጠራ ስትረቴጂ ከዚህ  አኳያ አልተመለከተውም፡፡ ከዩኒቨርስቲ የሚመረቁ ተማሪዎችን ስራ የማግኘት እድልን በተመለከተ ዘገባው "መንግስት ሁል ግዜ ተመራቂዎች ስራ ፈጣሪ እንጂ ስራ ፈላጊ ብቻ መሆን የለባችውም" የሚል መከራከሪያ እንደሚያቀርቡ ጠቅሶ፣ በዚህ ዙሪያ የፖለቲካ ተንታኞች አቀረቡት ያለውን ትችት ይገልፃል፡፡

የፖሎቲከኞቹ መከራከሪያ " ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ሕይወት የሚመራ ማህበረሰብ ውስጥ 'ስራ ፈጠራ' የሚለው የመንግስት መፈክር ዕውን ሊሆን አይችልም፤ አንድ ተመራቂ የስራ ዕድል ፈጣሪ ለመሆን በቂ መነሻ ካፒታል ሊኖረው ይገባል፡፡" የሚል ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት መንግስት የአገሪቱን የሰው ኃይል አቅም ለመፍጠርና ለማዳበር የሚያስችለውን ስትራቴጂ ቀርፆ ተግባራዊ ሲያደርግ ቢያንስ እንድ አስርት አመታትን ወደፊት አማትሮ በመመልከተ ነው፡፡  በአጭር ግዜ ውስጥ ሁሉንም ሰልጥኖ የወጣ የሰው ኃይል ማስተናገድ የሚያስችል የቅጥር ቦታ ሊኖር እንደማይችል ይታወቃል፡፡

ከስራ ፈጠራ ጋር በተገናኘ የተነሳውን በተመለከተ፣ ዕውቀት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ማለት በራሱ በተደላደለ የስራ ዕድል መጠቀም ላይ የተንጠለጠለ ማለት ብቻ ሳይሆን፣ ስራ መፍጠር/ ሃብት መፍጠር የሚችል ዜጋ ማፍራት የሚለውንም ያጠቃልላል። የላቀ ዕውቀት አለው ተብሎ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚወጣ ተማሪ፣ ስራ መፍጠርም የሚያስችል ዕወቀት አለው ተብሎ ነው የሚታሰበው። በዚህ ዙሪያ በአገራችን ያለው ችግር የአመለካከት ችግር ነው። ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች፣ ስራ መፍጠርም የሚያስችል አቀም ቢኖራቸውም እሰከ ቅርብ ግዜ ድረስ በአመዛኙ “ስራ መፈጠር አለብኝ” የሚል አመለካከትና የስነልቦና ዝግኝት አይታይባቸውም፡፡ የአብዛኛው ሕዝብ አመለካከትም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። “ይህ ለምን ሆነ?” የሚለው በተለይ ከኢትዮጵያ የትምህርት ታሪክ በተለይ ከዘመናዊ ትምህርት አጀማመረና ዕደገት እንዲሁም ከሰራ ባህላችን ጋር የተገናኘ በመሆኑ ሰፊ ጥናት ይፈልጋል። በመሆኑም ግዜና ሁኔታ ሲፈቅድ ለመመለስ በቀጠሮ እተወዋለሁ ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከሰራ ፈጠራ ጋር በተያያዘ ያለው ቀዳሚ ችግር ይህ የአመለካከት ችግር መሆኑ ሳይዘነጋ፣ ሪፖርተር በዘገባው “አንድ ተመራቂ የስራ ዕድል ፈጣሪ ለመሆን በቂ መነሻ ካፒታል ሊኖረው ይገባል፣ ከእጅ ወደአፍ የሆነ ህይወት በሚመራ ማህበረሰብ ውስጥ ስራ ፈጠራ የሚለው የመንገሰት መፈክር እውን ሊሆን አይቸልም” ብሎናል። አርግጥ ነው አንድ በአእምሮ ውስጥ ያለን የስራ ፈጠራ ውጥን ተግባራዊ ማድረግ፣ መሰረታዊ ከሆነው የዕውቀትና ጉልበት ግብዓት በተጨማሪ፣ ሌሎች ግብአቶቸንም ይፈልጋል። ይህ ደግሞ እነዚህን ግብዓቶች አግኝቶ ከዕውቀትና ጉልበት ጋር በማዋደድ ሃብት መፍጠር የሚያስችል ካፒታል (ረቢ ሃብት) ይፈልጋል። ይህ ረቢ ሃብት - ካፒታል ከፍጆታ በላይ የሆነ ተቆጥቦ የተከማቸ ሃብት ነው። በመሆኑም ገና ከዩኒቨርስቲ ተመረቆ ሰረቶ የመኖረን ዓለም የተቀላቀለ፣ እንኳን የሚቆጥበው፣ ከእጅ ወደአፍ የሚሆን የሌለው ዜጋ በአጁ ላይ ይህ ረቢ ሃብት የለውም፡፡

ይህ ግን መፍትሄ የሌለው ችግር አይደለም። በዕውቀት የተበጀ የስራ ውጥን፣ ውጥኑን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ዕውቀትና ጉልበት ያላቸው ሰዎች፣ ይህን ዕወን ማድረግ የሚያስችላቸውን ግብዓት ለማግኘት ገንዘብ መበደር ይችላሉ። መንግስት ይህን የብድር አገልግሎት ማግኘት የሚያስችል ዕድል አመቻችቷል። ስራ መጀመር ከሚያስችል ካፒታል ጋር በተያያዘ ለተነሳው ችግር በዚህ የብድር አገልግሎት መፍትሄ ተበጅቶለታል፡፡ አርቀው የሚያስቡና ባለራዕይ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂ ወጣቶች ደግሞ የስራ ፈጠራቸውን ዕወን ማድረግ የሚያስችላቸውን የራሳቸውን መላ የሚያበጁበት ሁኔታም አለ ። በአሁኑ ግዜ የተለመደው የባለራዕይ ወጣቶች አካሄድ፣ ከተመረቁበት ሞያ ውጭ ገንዘብ ማግኘት የሚያስችል የሽግግር ጊዜ ስራ ላይ መሰማራት ነው።

አሁን በኮብል ስቶን ጠረባና ንጣፍ ላይ ከተሰማሩት መሃከል በርካቶቹ ስራው የሚያስገኘውን አመርቂ ገንዘብ አስበው ለዋና ውጥን የፈጠራ ስራቸው የሚሆን የካፒታል ክምችት ለመፈጠር ወደዚህ ሰራ የገቡ ባለ ራዕይ ወጣቶች ናቸው። እስከ ዘለቄታው በኮብል ሰቶን ጠረባና ንጣፍ ስራ

ላይ ተሰማርተው ይኖራሉ ማለት ግን አይደለም፡፡ "የትምህርት ፖሊሲው ድንጋይ ጠራቢ እያፈራ ነው" የሚለውን ወቀሳ ከዚህ አኳያ ስንመለከተው ከግንዛቤ እጥረት አለያም ራዕይ ያላቸውን ወጣቶች ተስፋ ለማስቆረጥ የተነገረ ከመሆን ውጭ አይደለም፡፡ አንድ ሰው የተማረና በአካዳሚኩ ዓለም የተሻለ ዕውቀት ያለው ከሆነ ደግሞ ሥራውን አቅዶና ራዕይ ሰንቆ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ የተማረው ትምህርት የሚሰማራበትን ሥራ በዕውቀት የታገዘ ስለሚያደርገው የበለጠ ውጤታማ ሊያደርገው እንደሚችልና በቀጣይም ወደ ተሻለ ሌላ ዘርፍ ሊያድግና ሊለወጥ እንደሚችል ለምን ማሰብ ይሳነናል?

በዚሁ በከፍተኛ ትምህርት ተመራቂዎችና የስራ ዕድል  ዙሪያ ሌሎች ተቃዋሚ ፖለቲከኞችም አስተያየት ሰጥተዋል። የአንድነት ለፍትህና  ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራሮች የሆኑት አቶ አስራት ጣሴና ዶ/ር መራራ ጉዲና ከአስተያየት ሰጪዎቹ መሃከል ተጠቃሾቹ ናቸው። አቶ አስራት ጣሴ በጉዳዩ ላይ በሰጡት አስተያየት "አንድ ከዩኒቨርስቲ የወጣ ሰው ለምን ኮብል ስቶን ሰራተኛ ሆነ ተብሎ በወንጀል የማይጠየቅ ቢሆንም፣ ከትምህርት ዓላማ አንፃር ሲታይ ችግር እንዳለ ያሳያል" ብለዋል።

በቅድሚያ አንድን ሰው በኮብል ስቶን ስራ ላይ የመሰማራት መብት ያለው መሆኑን ለማመልከት "በወንጀል አይጠየቅም" የሚል አገላለፅ መጠቀማቸው በራሱ ፀያፍ ነው። ሰውየው ስራ ላይ ያላቸው አመለካከት በፊውዳል ኢትዮጵያ የስራ ባህል የተቃኘ መሆኑንም ያመለክታል። "በወንጀል አያስጠይቅ እንጂ ነውር ነው"  የሚል እንደምታ ያለው መሆኑም ሊስተዋል ይገባል። በአንድ የተለዬ ሙያ የተመረቀ ሆኖ በአጋጣሚ በሌላ የሥራ ዘርፍ ቢሰማራና በዚህም የተለዬና ተጨማሪ እውቀትና ልምድ ቢገበይ፤ሃብትና ንብረት ቢያፈራ፤የተሻለ ሕይዎት ቢመራ በግሌ  ችግሩ ምን ላይ እንደሆነ ሊገባኝ አይችልም፡፡ የዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ደግሞ ከመቶ ምን ያህል ፐርሰንት ሆኖስ ነው ይህ ችግር ያልሆነን ነገር እንደ ችግር በማንሳት ጉዳዩ የተለዬ ትርጉም እንዲይዝ የሚደረገው? የሥራን ክብርነትስ እንዴት አድርገን ነው ለትውልዱ የምናስተምረው?

አንድ ከዩኒቨርስቲ የወጣ ዜጋ በኮብል ስቶን ስራ ላይ መሰማራቱ ከትምህርት ዓላማ አንፃር ችግር እንዳለ ያሳየል በሚል የጠቀሱትን በተመለከተ፣ ከመንግስት የትምህርት/ የስልጣና ስትራቴጂ ዙሪያ ቀደም ሲል በሰጠሁት አስተያየት ምላሽ ለመስጠት የሞከርኩ ስለመሰለኝ አልደግመወም።

አንድ የሰለጠነ ሰው ፣ ራሱን ችሎ መኖር እንዳለበት የተገነዘበ፣ ይህን ማድረግ የሚያስችለውን በእጅ ያለ አማራጭ በሙሉ ለመጠቀም በአመለካከትም በስነልቦናም ዝግጁ የሆነ ማለት መሆኑን መገንዘብብም መልካም ይመስለኛል። ከዩኒቨርስቲ ሰልጥኖ የወጣ ኢትዮጵያዊ ደጅ ጠንቶ፣ የማይወራ አውርቶ ወደውጭ አገር ከሄደ በኋላ፣ ራሱን ችሎ ለመኖር በመኪና ጥበቃና እጥበት፣ መንገድ በመጥረግ፣በጥበቃ፤በሳህን እጥበትና ጽዳት፤በባሬስታነትና አስተናጋጅነት፤ ጋዜጣ በማዞር፤በፓርኪንግ፤በነዳጅ ቀጅነት፤ በዕቃ ማውረድና መጫን ….ስራ ላይ የሚሰማራ መሆኑ አሁን

አሁን ለብዙ ኢትዮጲያዊያን ገሃድ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ የተለመደና ምናልባትም ሁላችሁም የምታውቁት ቀልድ ለበስ አነጋገር ትዝ አለኝ፡፡ ይኸውም አሜሪካና አውሮፓ ያለን አበሻ "ሥራህ ምንድነው?" ብለህ አትጠይቀው የሚለው፡፡ እኛ አገር ዝቅተኛ ግምት የምንሰጠው አንዳንድ የሥራ ዓይነት ውጭ ሃገር ሲሰራ ግን የተከበረ አድርገን የምናይበት አመለካከት መታረም ይኖርበታል፡፡

ታዲያ በዚያ አገር ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁ ሰዎች በተጠቀሱትና መሰል ስራዎች ላይ መሰማራታቸውን ማንም እንደ ትልቅ ነውር አይቆጥረውም፡፡ በእነዚህ አገራት ሰዎች የሚታዘንላቸው ስራ ሲያጡ (ማንኛውንም አይነት ስራ) ብቻ ነው፡፡ ምንም ሳይኖራቸው ስራ የሚያማርጡ ደግሞ እንደነውረኛ ተቆጥረው ይናቃሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ከሌላ አገር የሚሄዱ ስደተኞችን ብቻ የሚመለከት አይደለም፤ የዜጎቻቸውም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡

ታዲያ አንድ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋም ተመርቆ የወጣ ኢትዮጵያዊ ራሱን እስኪለውጥ አለያም የተሻለ ስራ እስኪያገኝ በአገሩ ላይ በአነስተኛ ስራ ላይ መሰማራቱ እንደ ትልቅ ችግር ለምን ይታያል? በእርግጥ ማንም ሰው ቢሆን በተማረው ትምህርት ሥራ ላይ ተሰማርቶ የበለጠ ውጤታማ ቢሆን ተመራጭ መሆኑን አምናለሁ፤ይህ ተሟልቶ በማይገኝበት ሁኔታ ደግሞ ባለው ማንኛውም የሥራ አማራጭ በጊዜያዊነትም ይሁን በዘለቄታው መሳተፉ ጥቅም እንጂ አንዳችም ጉዳት ስለሌለው እንዳውም ይበልጥ ሊበረታታ ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡ ዋናው መመዘን ያለበት በተሰማራበት ሙያና ሥራ ምን ያህል ውጤታማ ነው የሚለው ቁምነገር ነው፡፡

ዶ/ር መረራም በዚሁ ጉዳይ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ “አንድ ሰው ችግር ከገጠመው ምንም ነገር ሰርቶ ሊኖር የሚችል ቢሆነም፣ እንዲህ ያለው ነገር ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል እጅግ ተስፋ አስቆራጭ ነው” ብለዋል፡፡ በቅድሚያ “አንድ ሰው ችግር ከገጠመው …” የሚለው፣ “አንድ ሰው የሌሎች ጥገኛ ሳይሆን ራሱን ችሎ ለመኖር …” በሚል አገላለፅ ቢቀርብ የስራን ክቡርነት ስለሚገልፅ ተገቢና ከተማረ ሰው የሚጠበቅ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው ችግር ሲገጥመው ልመናም ላይ ሊሰማራ ይችላልና፡፡ ሰርቶ የመኖርን ታላቅነትም የሚያንኳስስ ነው፡፡

በአነስተኛ ስራ ላይ መሰማራትን “ እንዲህ ያለው ነገር ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል ተስፋ አስቆራጭ ነው” በሚል የሰጡት አስተያየት የተማረ ሰው የመንግስት ቢሮክራሲን ለመሙላት የተዘጋጀ አድርጎ ከማየት በዘውዳዊው ስርዓት የተፈጠረ ያረጀ አመለካከት ነጸብራቅ ነው፡፡ ያለፈው ስርዓት አመለካከት ውርዴዎች የተማረ ሰው የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ቢሮ ካልያዘ ትምህርቱ የባከነ ሊመስላቸው ይችላል፣ የተለየ ስራ ላይ ተሰማርቶ ሲያዩት የመማር ዋጋ የተዋረደ ሊመስላቸው ይችላል፡፡ የዶ/ር መረራ  አስተያየት ከዚህ ያፈጀ አመለካከት ውርዴነት እንዳልተላቀቁ ያመላክታል፡፡ ሌሎችን ይቀይራሉ ብለን የምንጠብቃቸው ደ/ር መረራ ራሳቸውም አሮጌው አመለካከት ላይ ተቸንክረው የቀሩ መሆናቸው ደግሞ አሳዛኝ ነው፡፡

ዶ/ር መረራ ከዚሁ ጋር አያይዘው “ ያለውን ስራ ካድሬው ይቀራመታል፣ የተሻለ የትምህርት ስልጠና ያለውና ስራ ፈጣሪው ስደት ይሄዳል” በሚል ቧልት አዘል አሰተያየት አቅርበዋል፡፡ ዶ/ር መረራ ይህን ሲሉ፣ ልዩ ሙያ የሚጠይቀው፤ የአካውንቲንግ፣ የምህንድስና፣ የህግ … ስራዎች በካድሬዎች እየተሰራ ነው እያሉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የማይመስልና መሰረተ ቢስ ውሸት ነው፡፡ ከአጠቃላይ የመንግስት ሰራተኞች የኢህአዴግ አባላት ከ10 በመቶ የማይበልጡ ከመሆናቸው ጋር ሲታይ ደግሞ ውሸትነቱ ገጦ ይወጣል፡፡ ዶ/ር መረራ ወሬ አሳመርኩ ብለው ካድሬ መሃንዲስ ሆነ የሚል መጨበጫ የሌለው ቧልታቸውን ቢያቆሙ መልካም ነው፡፡ በአጠቃላይ የዶ/ር መረራ፣ የባልደረባቸው አቶ አስራትና የሌሎችም መሰል አስተያየቶች፣ በስራ ባሕላችን መለወጥ ሕዳሴ ላይ የተወረወሩ ትርጉም አልባ ትችቶች ናቸው፡፡